**የተከበሩ ወ/ሮ ፋንቱ ተስፋዬ !**

**የአማራ ብሔራዊ ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባኤ!**

**የተከበሩ ዶ/ር ይልቃል ከፋለ !**

**የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ-መስተዳድር!**

**የተከበራችሁ የም/ቤት አባላት!**

**ጥሪ የተደረገላችሁ እንግዶች!**

**ክቡራትና ክቡራን!**

በአማራ ብሔራዊ ክልል ሕገ-መንግስት አንቀጽ 116(2) እና የዋና ኦዲተር መ/ቤት እንደገና ማቋቋሚያ፣ ማደራጃና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 186/2003 አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 2 መ/ቤቱ በተሰጠው ስልጣን መሠረት የተከናወኑ ተግባራትን የሚገልጽ አጭር ሪፖርት ዋና ኦዲተሩ ለተከበረው ም/ቤት እንደሚያቀርብ ይደነግጋል፡፡ በዚሁ መሰረት በ2014 በጀት ዓመት በተመረጡ የክልሉ ተቋማት ላይ ከተጠናቀቁት አስራ አምስት የክዋኔ ኦዲት ሥራዎች የአስራ ሁለቱን አጭር ሪፖርት ለተከበረው ጉባዔ እንደሚከተለው አቀርባለሁ፡፡

1. በዚህ ሪፖርት ውስጥ የተካተቱት 2 ልዩ፣ 6 መደበኛ እና 4 የክትትል ኦዲት ሥራዎች ሲሆኑ ለመጥቀስ ያክልም፡-

   - ✓ ሁለቱ ልዩ የክዋኔ ኦዲት ሥራዎች የደ/ታቦር ከተማ ልማት ቤቶች ኮንስትራክሽን አገልግሎት ጽ/ቤት (አላግባብ የተከፈለ የግንባታ ክፍያ ለማረጋገጥ የተከናወነ ልዩ ኦዲት) እና የፋግታ ንዑስ ማዘጋጃ ቤት (ስራ ሳይሰራና ግዥ ሳይፈፀም ሃሰተኛ ሰነዶችን በማዘጋጀት አላግባብ ወጪ የተደረገ ገንዘብን ለማረጋገጥ የተከናወነ ልዩ ኦዲት) ሲሆኑ፤
   - ✓ ስድስቱ መደበኛ የክዋኔ ኦዲት ሥራዎች የገጠር መንገድ ኮንስትራክሽን ኤጀንሲ (ግብዓት ግዥ፣ አጠቃቀምና አስተዳደር እንዲሁም የመንገዶች ግንባታ አፈፃፀም)፤ የአብክመ ጤና ቢሮ (የጤና ተቋማት ግንባታ አፈጻጸም እና ውጤታማነት)፤ የፍኖተሰላም እና የእንጅባራ ከተማ አስተዳደሮች (የመሬት ሊዝ አስተዳደር ስርዓት)፤ በመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ልማት ቢሮ (የመስኖ ግንባታ አፈጻጸምና ውጤታማነት) እንዲሁም የአብክመ መሬት ቢሮ (የመሬት አስተዳደር፣ አጠቃቀምና ኢንቨስትመንት ስርዓት ውጤታማነት)፤

- ✓ አራቱ የክዋኔ ክትትል ኦዲት ሥራዎች ደግሞ የደ/ብርሃን ከተማ ልማት ቤቶች ኮንስትራክሽንና ገቢዎች ጽ/ቤት (የሊዝ ሂሳብ አያያዝ ሥርአት) ፣ የጐንደር ከተማ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ጽ/ቤት(የመጠጥ ውሃ አቅርቦትና ንብረት አስተዳደር) ፣ የአማራ መንገድ ስራዎች ድርጅት (የግንባታ ሥራዎች፣ ግብአት ግዢ፣ አቅርቦትና አስተዳደር) እና የአማራ ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት (የግንባታ አፈጻጸም፣የግዢና ሃብት አስተዳደር ሥርአት) በዚህ ሪፖርት የተካተቱ ናቸው፡፡

2. የእያንዳንዱን የመደበኛ የክዋኔ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤት ዝርዝር ውጤትና የማሻሻያ አስተያየት የያዘ የኦዲት ሪፖርት ለየመ/ቤቶችና ለተቆጣጣሪ አካላት አስቀድሞ እንዲደርሳቸው የተደረገ ሲሆን የልዩ ኦዲቶችን ደግሞ ለፍትህ አካላትና ለየሚመለከታቸዉ ተቆጣጣሪ መ/ቤቶች ልከናል፡፡ የመደበኛ ኦዲት ሪፖርት ከተላከላቸውና ምላሽ መስጠት ከሚጠበቅባቸው 6 ኦዲት ተደራጊ ተቋማት 2ቱ በወቅቱ ምላሽ የሰጡ ሲሆን ቀሪዎቹ 4 ተቋማት (የአብክመ ጤና ቢሮ፣ የአብክመ መሬት ቢሮ፣ የፍኖተሰላም ከተማ አስተዳደር እና የእንጅባራ ከተማ አስተዳር) ይህ የዘገባ ሪፖርት ለምክርቤት እስከተላከበት 13/3/2015 ዓ.ም ድረስ ምላሽ አልሰጡም፡፡

3. ለክዋኔ ኦዲት ሥረ መሠረት የሆኑት መንግስት ያወጣቸው ፖሊሲና ስትራቴጂዎች፤ ለኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች በህግ የተሰጣቸው ስልጣንና ተግባራት፣የመ/ቤቶች የሥራ ዕቅድና የአፈፃፀም ሪፖርቶች እንዲሁም በየደረጃው ያሉ የሚመለከታቸው ሠራተኞችና ኃላፊዎች የሰጧቸው ምላሽ እና ማብራሪያዎች ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ እንደአስፈላጊነቱ ከ3ኛ ወገኖች የተገኙ ብቃትና ተቀባይነት ያላቸው ማስረጃዎች በኦዲት ስራው ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ የኦዲት ስራውም ዓለም አቀፍ እና አገራዊ የክዋኔ ኦዲት አሰራር መርሆችና ስታንዳርዶችን ተከትሎ የተከናወነና ግኝቶቹም አስተማማኝና ተጨባጭ ማስረጃዎች ያሏቸው ናቸው፡፡ በአጠቃላይ በዚህ ሪፖርት ላይ የቀረቡት ግኝቶች በመደበኛ ኦዲት ሥራዎች የተለመደውን አልፎ አልፎ ወይም በንሞና ኦዲት ስልት በመከተል በተመረጡ ርዕሰ ጉዳዩች በክልል ቢሮዎች፣ ዞኖችና ከተሞች እንዲሁም ወረዳዎች ሲሆን በልዩ ኦዲት ሥራዎች ዝር ዝር ወይም ሙሉ በሙሉ የኦዲት ምርመራ ስልት በመጠቀም ነው፡፡

## ልዩ የክዋኔ ኦዲት ስራዎች፡-

### በደብረታቦር ከተማ አስተዳደር ከተማ ልማት ቤቶች ኮንስትራክሽን አገልግሎት ጽ/ቤት አላግባብ የተከፈለ የግንባታ ክፍያ ለማረጋገጥ የተከናወነ ልዩ ኦዲት

**(ለኦዲቱ መነሻ የሆነዉ የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ፍትህ ቢሮ ያቀረበው ጥቆማ ነዉ፡፡)**

4. በ2012 በጀት ዓመት የደብረታቦር ከተማ አስተዳደር ከተማ ልማት ቤቶች ኮንስትራክሽን አገልግሎት ጽ/ቤት ከልጅቱ ማሪያም ኮብልስቶን መንገድ እስከ ዋናው አስፓልት ድረስ እና ከቀበሌ 01 እያያ ገላው ፈንቴ አወቀ ከብት በረት እስከ ልጅቱ ማሪያም ኮብልስቶን ድረስ ለሚያሰራቸው ሁለት የገረጋንቲ ጠጠር መንገድ ስራዎች ባወጣው ግልፅ ጨረታ መሰረት ተፈላጊውን የቴክኒክ መመዘኛ መስፈርት ያሟሉ ተጫራቾች ባቀረቡት የመስሪያ ጠቅላላ የገንዘብ መጠን መሰረት ለመጀመሪያው መንገድ አንድ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ ዝቅተኛ የመስሪያ ዋጋ ብር 6,603,888.11 ለሁለተኛው መንገድ ሌላ ተቋራጭ ብር 2,372,546.58 ያቀረቡ ቢሆንም ጨረታውን አሸናፊ ሆነው ሳይመረጡ መስሪያ ቤቱ ለሌላ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ አሸንፏል በሚል የመጀመሪያውን መንገድ በብር 14,657,664.99 ሁለተኛውን መንገድ በብር 9,188,161.58 እንዲገነባቸው በደብረታቦር ከተማ አስተዳደር ፍትህ ጽ/ቤት ውል የተያዘ በመሆኑ በተገባው ውል መሰረት ለተሰራ ስራ ለመጀመሪያው መንገድ ብር 14,018,406.86 ለሁለተኛው መንገድ ብር 8,763,031.31 በወጪ ፀድቆ የተከፈለ በመሆኑ በልዩነት በመጀመሪያው መንገድ ግንባታ ብር 7,414,518.75 ለሁለተኛው መንገድ ግንባታ ብር 6,390,484.73 ያለአግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

4.1 በመሆኑም በአብክመ የግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 179/2003 እና በአብክመ የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 1/2003 ከጨረታ ውጭ የሚያደርጉ ዋና ዋና ጉዳዮችን (rejection criteria) በጨረታ ሰነዱ ላይ በግልፅ ተጫራቾች እንዲያውቋቸው መደረግ አለበት፤ ይህ ባልሆነበት ሁኔታ ተጫራቾችን መሰረታዊ ነገሮችን አላሟሉም በሚል ከጨረታ ውጭ ማድረግ አይፈቀድም በሚል የተገለጸ ቢሆንም የጨረታ ገምጋሚ ኮሚቴው በጨረታ ሰነዱ ውስጥ ከጨረታ ውጭ የሚያደርጉ ዋና ዋና ጉዳዮችን (rejection criteria) ባላስቀመጠበት ሁኔታ እና የቴክኒካል መመዘኛ መስፈርት መወዳደሪያ ፖስታው ተከፍቶ ዝቅተኛ የቴክኒክ መመዘኛ መስፈርቱን (70%) ያሟሉ ተጫራቾች ከተለዩ በኋላ አሸናፊ መሆን የሚገባቸው ተቋራጭ

ስለድርጅታቸው ያቀረቡት የፋይናንስ አቋም የሚገልፅ ማስረጃ የተሳሳተ ነው በሚል ቀድሞ ባልተሳለፈ መመዘኛ ከጨረታ ውጭ በማድረግ አንድን ስራ ተቋራጭ ያለአግባብ እንዲያሸንፍ ተደርጎ ሥራዎች በመሰጠታቸው በድምሩ በልዩነት ብር 13,805,003.48 ያለአግባብ የተከፈለ የግንባታ አገልግሎት ግዥ ወጪ ሆኖ በኦዲት ተገኝቷል፡፡

## በፋግታ ንዑስ ማዘጋጃ ቤት ስራ ሳይሰራና ግዥ ሳይፈፀም ሃሰተኛ ሰነዶችን በማዘጋጀት አላግባብ ወጪ የተደረገ ገንዘብን ለማረጋገጥ የተከናወነ ልዩ ኦዲት፤

(የኦዲቱ መነሻ የሆነዉ የአዊ ብሔረሰብ አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የክዋኔ ኦዲት እንዲደረግ የሰጠው ትዕዛዝ ነዉ፡፡)

5. በፋግታ ንዑስ ማዘጋጃ ቤት ለመናኸሪያ አጥር ጥገናና ውስጥ ማስተካከያ፣ በከተማው የባህርዛፍ ጉቶ ማስነቀያ የጉልበት ክፍያ፣የከብት ማገቻ በረትና አጥር ማሰሪያ የጉልበት ክፍያ፣ የህዝብ መጸዳጃ ቤት ማሰሪያ የጉልበት ክፍያ፣ ለውስጥ መንገድ ጥገናና ቦይ ተፋሰስ ቁፋሮ የጉልበት ክፍያ ፣ለአሸዋ መግዥያ፣ ለመናኸሪያ የአጥር እንጨት መግዥያ፣ ለፎቶ ኮፒ አገልግሎት እና በብልጫ የጸደቁ የሬዳሽ አሸዋ ግዥና የመነኸሪያ በር የአናጺ የጉልበት አገልግሎት ግዥ ክፍያ በሚል ስራ ሳይሰራና ግዥ ሳይፈፀም ሃሰተኛ ሰነዶችን በማዘጋጀት አላግባብ በድምሩ ብር 437,469.00 ወጪ ተፈጽሞ በኦዲት ተገኝቷል፡፡

**የተከበሩ አፈ-ጉባኤ!**

**የተከበሩ ርዕሰ መስተዳድር!**

**የተከበራችሁ የም/ቤት አባላት!**

**ጥሪ የተደረገላችሁ እንግዶች!**

**ክቡራትና ክቡራን!**

## መስሪያ ቤታችን በመደበኛ አቅዶ የፈጸማቸው የክዋኔ ኦዲት ስራዎችና ዋና ዋና ግኝቶቻቸው የሚከተሉት ናቸው ፡-

### የአብክመ ገጠር መንገድ ኮንስትራክሽን ኤጄንሲ የመንገዶች ግንባታ አፈፃፀም፣ የግንባታ ግብዓት ግዥና አጠቃቀም

6. በክልሉ እየተገነቡ ያሉ የገጠር መንገዶች በተያዘላቸው የግንባታ ጊዜ ተጠናቀው አገልግሎት መስጠት ሲገባቸው ከ2004 እስከ 2013 በጀት አመት በብር 1,467,480,814.88 ወጪ እየተገነቡ ካሉት 33 የገጠር መንገዶች መካከል ብር 1,218,070,270.92 (83%) የወጪ ድርሻ ያላቸው 15 የገጠር መንገዶች መጠናቀቅ ከነበረባቸው ጊዜ ከ1 እስከ 5 አመትና በላይ የዘገዩና እስከአሁንም በግንባታ ላይ ያሉ መሆናቸው መንገዶች በተያዘላቸው ጊዜ ተጠናቀዉ ለማህበረሰቡ አገልግሎት እንዳይሰጡ ያደረገና የመንገዶች ግንባታ በዘገየ ቁጥር ኤጀንሲው ለሌሎች ግንባታዎች ማዋል የሚችለውን የአስተዳደር እና የአፈጻጸም ወጪ በዘገዩት መንገዶች ላይ ብቻ እንዲያወጣ በማድረግ ለከፍተኛ ወጪ የሚዳረግ አሰራር ከመሆኑም በላይ የመንገድ ግንባታው መዘግየትና አለመጠናቀቅ በአካባቢው የኢኮኖሚና ማህበራዊ እንቅስቃሴ ላይ ተጽዕኖ እንደሚኖረውና በዝናብ ወቅት በሚከሰት ጎርፍ መንገዶች ጉዳት ስለሚደርስባቸው ለመልሶ ግንባታና ለተደጋጋሚ የጥገና ወጪ የሚዳርግ አሰራር መሆኑ፤

7. የኤጀንሲው የኪራይ ማሽኖች፣ ተሽከርካሪዎችና መሳሪያዎች አጠቃቀምና አስተዳደር ስርዓት የተቋሙን ጥቅም በሚያስጠብቅ መልኩ ተግባራዊ ሊደረግ ሲገባ በ2013 በጀት ዓመት ኤጀንሲው ተከራይቶ ጥቅም ላይ ካዋላቸው ማሽኖችና ተሽከርካሪዎች መካከል 11ዱ በንሞና ተወስደው በተደረገ ምርመራ በጨረታ አሸንፈው ለመስራት ውል ከገቡባቸው አስቸጋሪ ቦታዎች ወደ ተሻለና ተጫራቾች በዝቅተኛ ዋጋ ወደሚሰሩበት ቦታ ተዛውረው ነገር ግን በመጀመሪያ ባሸነፉበት የአስቸጋሪ ቦታዎች

ከፍተኛ ዋጋ እየተከፈላቸው እንዲሰሩ በመደረጉ ብር 475,318.74 በልዩነት የመንግስትን ጥቅም ያሳጣ አሰራር መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

8. የአብክመ ገጠር መንገድ ኮንስትራክሽን ኤጀንሲ ለአብክመ ገንዘብ ቢሮ በደብዳቤ በጠየቀው መሰረት 7 ዶዘሮች በቀድሞው የአብክመ የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ኤጀንሲ ግዥ የተከናወነ ሲሆን ግዥው በተቋማችን ኦዲት ሲደረግ ጨረታውን ያሸነፉት ተወዳዳሪ ከተዘጋጀው መለያ ባህሪያት (specifications) ውስጥ 13ቱን መለያ ባህሪያትን ባላሟሉበት ሁኔታ ተጫራቹ አሟልተው እንዳቀረቡ እና ዝቅተኛውን የመመዘኛ መስፈርት እንዳሟሉ ተደርጎ ዝርዝር መመዘኛዎች ላይ ውጤት የተሰጠና ግዥው የተከናወነ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

8.1 እነዚህ በ2012 ዓ.ም ተገዝተው ገቢ የተደረጉ ዶዘሮች የነዳጅ ፍጆታቸው ኦዲት ሲደረግ ከፍተኛ እንደሆነና ፍጆታቸው እስከ አስራ አምስት ሺህ ሰዓት ከሰሩት ነባር ዶዘሮች ጋር ሲነጻጸር እስከ 12 ሊትር በኪሎ ሜትር የፍጆታ ብልጫ እንዳላቸው፤ የሥራ አፈጻጸም አቅማቸውም በዓመት ከሚጠበቅባቸው በ50% ያነሰ መሆኑ በኦዲት ታይቷል፡፡

8.2 የጉልበት ማነስ ፤የሞተር ሙቀት መጨመር፤ተደጋጋሚ ብልሽት ማጋጠም፤የመሪ አለመታዘዝ ፤የፍሬን አለመያዝ፤የብናኝ መከላከያ መዝጊያዎች ቶሎ ቶሎ መላላት፤የነዳጅ ማስተላለፊያ መስመሮች ብልሽት፤የጭስ መጥቆር፤መለዋወጫ እቃዎችን ገበያ ላይ ለማግኘት መቸገር እና የነዳጅ ታንከሩ የተሰራበት ጥሬ ዕቃ ዝገት የሚከላከል ባለመሆኑ በሚፈጠረው የዝገት ቁርጥራጮች የነዳጅ ማስተላለፊያ መስመሮችን እየዘጋ መቸገር በተገዙት ዶዘሮች ላይ የተስተዋሉ ችግሮች ናቸው፡፡

8.3 በአጠቃላይ ሲታይ ለገጠር መንገድ ኮንስትራክሽን ኤጀንሲ በቀን 01/12/2012 ዓ.ም ገቢ የተደረጉት 7 *LiuGong* ዶዘሮች ግዥ አቅራቢው ለግዥ የተዘጋጀውን መለያ ባህሪይ (specification) ባላሟላበት ሁኔታ ተገዝተው መቅረባቸው የክልሉን የግዥ መመሪያ ያልጠበቀና መንግስት ለማሽኖች ግዥ ያወጣውን ብር 74,155,821.19 ተመጣጣኝ የአገልግሎት ተጠቃሚነትን ያሳጣ መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

9. በሌላ መልኩ በኤጀንሲው ለግንባታ የሚያገለግሉ ማሽኖች እና ተሽከርካሪዎች በብልሽት ሲቆሙ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተጠግነው ወደ ስራ እንዲገቡ በማድረግ ስራዎች እያከናወነ መሆኑ ኦዲት

ሲደረግ የኤጀነሲው ንብረት የሆኑ 2 ዶዘሮች፣ 3 የመንገድ ሮለሮች፣ 3 ገልባጭ መኪኖች እና አንድ ባለ አንድ ጋቢና ተሽከርካሪ ከቀላል ብልሽት ጀምሮ በገጠሙ ችግሮች ምክንያት ከአንድ ዓመት ተኩል እስከ 10 ዓመት ያለአገልግሎት የቆሙ መሆኑ በኦዲት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

## የአብክመ ጤና ቢሮ የጤና ተቋማት ግንባታ አፈጻጸም እና ውጤታማነት፤

10. የደ/ብርሃን፣ የደብረ ማርቆስና የፍኖተ ሰላም ሪፈራል ሆስፒታሎች ግንባታ በ2009 ዓ.ም ለተለያዩ 3 ተቋራጮች በብር 739,260,392.00 የግንባታ ውል የተሰጠና በተያዘው ውል መሰረትም ግንባታቸው ከ1324 ቀናት በኋላ በ2013 አጋማሽ ላይ እንደሚጠናቀቅ ስምምነት የተደረሰበት ቢሆንም ኦዲት እስከተደረገበት ግንቦት 2014 ዓ.ም ድረስ የሪፈራል ሆስፒታሎቹ ግንባታ ከ50% በታች አፈጻጸም ላይ ያሉ መሆኑ በኦዲት ታይቷል፤

11. የፈለገ ህይወት ሪፈራል ሆስፒታል እናቶችና ህጻናት የሕክምና አገልግሎት መስጫ ማዕከል ግንባታ በ2006 ዓ.ም ለአንድ ኮንትራክተር በብር 208,376,301.55 ውል ተይዞ ግንባታዉ ቢጀመርም 54.02% እንደደረሰ ግንባታዉ የቆመ መሆኑ፤

12. የባህር ዳር አእምሮ ህሙማን ማገገሚያ ግንባታ ለአንድ ኮንትራክተር በብር 134,918,326.42 በተያዘው ውል መሰረት በ2013 ዓ.ም እንደሚጠናቀቅ የተገለጸ ቢሆንም ግንባታዉ 37% ደርሶ የቆመ መሆኑ፤

13. በምዕራብ ጎጃም ዞን በ2009 ዓ.ም 12 የጤና ጣቢያ ደረጃ ማሳደግ ግንባታ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ጊዜ ያልተጠናቀቁና ሥራቸው የተቋረጠ መሆኑ፣ በ2012 በጀት ዓመት ግንባታቸው ከተጀመሩት 17 የጤና ተቋማት የግንባታ ፕሮጀክቶች መካከል 3 ፕሮጀክቶች ግንባታቸው የቆመ መሆኑ፤ የጤና ጣቢያ የባለሙያዎች መኖሪያ ቤት ግንባታ በ2012 ዓ.ም እንደሚጠናቀቅ ውል የተያዘ ቢሆንም ግንባታው ያልተጠናቀቀ መሆኑ፣

14. በደቡብ ጎንደር ዞን ከ2009 እስከ 2012 በጀት ዓመት የተገነቡ እና እየተገነቡ ካሉ 72 የጤና ተቋማት ግንባታ ፕሮጀክቶች ውስጥ 56 የጤና ተቋማት ፕሮጀክቶች በአሰሪ መ/ቤቶች እና በሥራ ተቋራጮች በተደረገው የውል ስምምነት መሰረት በተያዘላቸው ጊዜ ያልተጠናቀቁ መሆናቸው በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

15. በ2010 በጀት አመት የደብረ ታቦር ሪጅናል ላብራቶሪ ግንባታ ከአንድ ስራ ተቋራጭ ጋር ውል ተይዞ በ2011 ዓ.ም እንደሚጠናቀቅ የተገለጸ ቢሆንም ግንባታዉ 85% ላይ ደርሶ የቆመ መሆኑ፤

16. የመጀመሪያው ሥራ ተቋራጭ የግንባታ ሥራ ውለታ ተቋርጦ ለሌላ የስራ ተቋራጭ ሲሰጥ የቅድመ ክፍያ፤ የውል ማስከበሪያ መያዣ እና ቅጣት ሊሰበሰብ ሲገባ በ15 የግንባታ ፕሮጀክቶች ማለትም በደቡብ ወሎ ዞን የመህል ሳይንት የመጀመሪያ ሆስፒታል፣ የጎንደር ዞናል ሆስፒታል፣ በቡሬ ዙሪያ ወረዳ የአለፋ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ የእናቶች ማቆያ፣ የፍኖተ ሰላም ሆስፒታል መፀዳጃ ቤት፣ በጃቢጠህናን ወረዳ በአስዋ ጤና ጣቢያ ውስጥ የባለሙያዎች መኖሪያ፣ የአዴት ጤና ጣቢያ እናቶች ማቆያ፣ ቲቢ ክፍል፣ ፋርማሲና መፀዳጃ ቤት፣ በባ/ዳር ዙሪያ ወረዳ የቅምባባ መለስተኛ ቀዶ ጥገና፣ በቡሬ ከተማ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ የአጥር ስራ ግንባታ፣ የጉሌ ጤና ጣቢያ ባለ 5 መቀመጫ መጻዳጃ ቤት፣ የጉለም ጤና ጣቢያ የአጥር ስራ ግንባታ፣ እብናትና እስቴ ወረዳዎች የጤና ጣቢያ ደረጃ ማሳደግ ፕሮጀክቶች፣ በአንዳቤት ወረዳ አጸደ ማሪያም ጤና ጣቢያ የደረጃ ማሳደግ ግንባታ እና በእሰቴ ወረዳ የደስቋ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ ሎት አንድ ደረጃ ማሳደግ ግንባታ ከ 23 - 85 በመቶ የግንባታ ደረጃ ላይ ደርሰው በተቋራጮች ጥፋት የተቋረጡ በመሆኑ ከተቋራጮቹ በህግ አግባብ መሰብሰብ የነበረበት የቅድመ ክፍያ ብር 12,108,889.31፣ የውል ማስከበሪያ መያዣ ብር 17,599, 457.99 እና ቅጣት ብር 16,827,660.57 በድምሩ ብር 46,536,007.87 የኦዲት ሥራው እስከተጠናቀቀበት ግንቦት 2014 ዓ.ም ድረስ ያልተሰበሰበ መሆኑ በኦዲት ምርመራው ተረጋግጧል፡፡

17. በመሆኑም ቢሮዉ ያሉበተን የውለታ አያያዝና አስተዳደር ውስንነት በመፍታት፤ የጠራና ያለቀለት ዲዛይን ሳይዝ ሥራ ባለመጀመር ፣ የፕሮጀክቶች ስራ አቀናጅቶ በመምራትና የክትትል እና የድጋፍ ሥራዎችን በማጠናከር ከግንባታዎች ጋር ተያይዘው ለተከሰቱ እና ለሚከሰቱ ችግሮች ፈጣን ምላሽ እየሰጡ በወቅቱ ማጠናቀቅ እንደሚገባ ፤

18. እንዲሁም ለጤና ተቋማት የግንባታ ፕሮጀክቶች የቅድመ ክፍያ፣ የውል ማስከበሪያ መያዣ እና ቅጣት ገንዘብ በህግ አግባብ እንዲሰበሰብ ቢሮዉ ተገቢዉን ጥረት ሊያደርግ እንደሚገባ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

## የፍኖተ ሰላም ከተማ አስተዳደር ከተማና መሰረተ ልማት ጽ/ቤት እና ገቢዎች ጽ/ቤት የሊዝ አስተዳደር ስርዓት

19. የሊዝ ደንበኞች ሲጫረቱ በሞሉት ዋጋ መሰረት የቅድሚያ ክፍያ እየከፈሉ ዉል መያዝ ሲገባቸዉ ከ2007 እስከ 2009 ዓ.ም በሊዝ ጨረታ ከተላለፉት መሬቶች መካከል 9 የሚሆኑት ተጫራቾች ባሸነፉበት ሳይሆን ያነሰ የቅድሚያ ክፍያ ዋጋ እንዲከፍሉ ተደርጎ ውል በመያዙ መንግስት በወቅቱ ሊያገኘው የሚገባውን ብር 222,835.40 ያሳጣ መሆኑን በኦዲት ምርመራ ተረጋግጧል፡፡

20. ሁኔታዉ ጽ/ቤቱ የሊዝ ቅድሚያ ክፍያ ገንዘብ በአግባቡ ባለመሰብሰቡ መንግስት ከመሬት ሽያጭ ማግኘት የሚገባዉን ገቢ እንዳያገኝ እና ለግለሰቦች መጠቀሚያነት እንዲዉል ያደረገ በመሆኑ የከተማው የመሰረተ ልማት ትግበራ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚያሳድር ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

21. የሊዝ ደንበኞች ጨረታ ባሸነፉበት ዋጋ መሰረት የሊዝ ዉል መያዝ ሲገባቸዉ በ2008፣ 2010 እና 2012 በጀት ዓመት መሬት ለ3 ደንበኞች ሲተላለፍ በካሬ ሜትር የተጫረቱበት ቀርቶ እስከ ብር 474 ለካሬ ሜትር በሚደርስ ልዩነት ዝቅ ተደርጎ ውል በመያዙ ብር 329,583.00 መንግስት ጥቅም እንዲያጣ ተደርጓል፡፡ ይህም የተደረገው ሰነዶችን በመሰረዝና በፍሉድ አጥፍቶ በማስተካከል እንዲሁም ከፍተኛ ዋጋ የሞሉትን በመተው ዝቅተኛ ዋጋ ለሞሉት በመሰጠቱ መሆኑን የኦዲት ግኝቱ ያሳያል፡፡

22. ከ2007 እስከ 2013 ዓ.ም ባሉት ጊዜያት ጠቅላላ ስፋታቸው 44,874.75 ካ.ሜ የሆነ 30 ቦታዎች ተጫራቾች የሊዝ ክፍያዉን ከፍለው ለማጠናቀቅ ከተወዳደሩበት ዓመት በላይ ከ2 እስከ 46 ዓመት ተራዝሞ በውል ሰነዱ ላይ በመሞላቱ የኦዲት ሥራው እስከተከናወነበት ባለው ጊዜ ብቻ መንግስት ሊሰበስበው የሚገባውን ብር 3,277,278.26 ያሳጣ መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

## በእንጅባራ ከተማ አስተዳደር ከተማና መሰረተ ልማት ጽ/ቤት እና ገቢዎች ጽ/ቤት የሊዝ ሂሳብ አስተዳደር ስርዓት

23. የሊዝ ደንበኞች ጨረታ ባሸነፉበት ዋጋ እና የካሬ ሜትር መጠን መሰረት ዉል መያዝና እና የዉል ስምምነትና ሌሎች ሰነዶች በአግባቡ መጠበቅ ሲገባቸዉ በእንጅባራ ከተማ በ2008 በጀት ዓመት በወጣው የመሬት ሊዝ ጨረታ ማሸነፍ የነበረበት የመጀመሪያው ሆኖ እያለ 2ተኛ ዝቅተኛ ዋጋ አቅራቢ ለሆነው በመሰጠቱ፣ እንዲሁም በ 2010 በጀት ዓመት በወጣው የመሬት ሊዝ ጨረታ አንደኛ የወጡት ግለሰብ ቀርበው ውል ሳይዙ በመቅረታቸው ሶስተኛ የወጡት ግለሰብ ውል ሲይዙ ውላቸው አንደኛ የወጡት ባቀረቡት ዋጋ መሞላት ሲገባው ራሳቸው ሶስተኛ የወጡት ሲወዳደሩ በሞሉት ዋጋ ውል በመያዙ እንዲሁም ዓመታዊ ቀሪ የሊዝ ክፍያ መያዝ ከሚገባው ዝቅ ብሎ በመያዙ መንግስት የሚያገኘውን ብር 4,955,200.00 ያሳጣ መሆኑ የኦዲት ምርመራ ውጤቱ ያሳያል፡፡

24. በሊዝ መመሪያ መሰረት መሬት የተረከበ አካል የግንባታ ፈቃድ ከወሰደበት ቀን ጀምሮ እንደግንባታዉ ደረጃና አይነት በ24 ወይም በ36 አልያም በ48 ወራት ማጠናቀቅና መሬቱን ለታለመለት ዓላማ ብቻ ማዋል የገባዋል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን የሊዝ ውሉን በማቋረጥ መሬቱ ሊነጠቅ ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ በከተማ አስተዳደሩ መሰረተ ልማት ጽ/ቤት በናሞና ከታዩት መካከል አንድ የሊዝ ደንበኛ 476 ካሬ ሜትር ቦታ በሊዝ መነሻ ዋጋ በካሬ ሜትር ብር 41.02 ጠቅላላ ዋጋ ብር 19,525.52 ለማኑፋክቸሪንግ ኢንቨስትመንት አገልግሎት መሬት በምደባ የወሰዱ ሲሆን መሬቱን አላአግባብ ከህግ ዉጭ ለሌላ አካል በብር 400,000.00 የሸጡና እንደገና ያው መሬት ወደ 3ተኛ ወገን በብር 1,000,000.00 ተላልፎ የተገኘ መሆኑ፡፡ ሁለቱንም ጊዜ የስመ ንብረት ዝውውሩ በአንድ ባለሙያ የተፈፀመ መሆኑን የኦዲት ምርመራ ውጤቱ ያመለክታል፡፡

## የአብክመ መሬት ቢሮ የገጠር መሬት አስተዳደር፣ አጠቃቀምና ኢንቨስትመንት ስርዓት ውጤታማነት፤

25. ባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ እና ሰሜን አቸፈር ወረዳ 5 የተለያዩ ድርጅቶች (አስፓራጋስ፣ኢትዮ ማጂክ ፎረም፣ዲጄ ኢትዮጵያ፣ኤግል ሮዝስና ኤ.ኬ የተባሉ) ከ2009 ዓ.ም ጀምሮ ስፋቱ በድምሩ 280 ሄ/ር የሚደርስ መሬት ለአበባ እርሻ ልማት ተረክበው የነበረ ቢሆንም ኦዲቱ እስከተከናወነበት 2014 ዓ.ም ድረስ መሬቱን ያላለሙበትና እርምጃም ያልተወሰደባቸው መሆኑን በኦዲት ምርመራው ማረጋገጥ ተችሏል።

26. በአንጎለላና ጠራ ወረዳ ጨኪ ቀበሌ አንድ ግለሰብና አንድ ማህበር በ2008 በጀት ዓመት በድምሩ 7 ሄ/ር መሬት ተረክበው ለታለመለት ዓላማ ባለማዋላቸው ምክንያት በ2010 ዓ.ም መሬቱ ተነጥቆ ወደ መሬት ባንክ እንዲገባ ውሳኔ የተሰጠ ቢሆንም ሳይነጠቁ በመቅረቱ መሬቱን ለሌላ ዓላማ እየተጠቀሙበት መሆኑ፤

27. በወንበርማ ወረዳ ባለሃብቶችና ማህበራት ለሰብል ልማት ከተሰጣቸው 384.3 ሄ/ር ውጪ 189.7 ሄ/ር መሬት ደን በመጨፍጨፍ ጭምር አላግባብ በህገወጥ መንገድ ይዘው የተገኙ መሆኑ፤

28. በጃቢ ጠህናን ወረዳ እና በደንበጫ ወረዳ 3 ባለሃብቶች 174.93 ሄ/ር መሬት ለሰብል ልማት ተግባር ለማዋል ውል ወስደው የተረከቡትን መሬት ለ3ኛ ወገን አከራይተው መገኘታቸው፤ በኦዲት ምርመራ ታይቷል።

29. ከ2008 በጀት ዓመት ጀምሮ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውሉ የኢንቨስትመንት ቦታዎች ተረክበው እያለ ምንም አይነት ግንባታ ያልጀመሩና አጥረው የያዙ 26 ፕሮጀክቶች እንዲሁም ግንባታ ጀምረው ያላጠናቀቁ /ያቋረጡ/ 22 ፕሮጀክቶች በሰሜን ሸዋ እና ምዕራብ ጎጃም ዞኖች በተደረገ የክዋኔ ኦዲት ተገኝተዋል።

30. በሰሜን ሸዋ ዞን አስተዳደር ለኢንቨስትመንት መሬት ከተረከቡ ባለሀብቶች የመሬት ኪራይ በወቅቱ እየተሰበሰበ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ 3 በኢንቨስትመንት የተሰማሩ ባለሀብቶች የሊዝ ውላቸው አልተገኘም፤ በግብርናና ከግብርና ውጭ በሆነ ኢንቨስትመንት ሥራ ላይ የተሰማሩ 39 ባለሀብቶች የመሬት ኪራይ ውል ለገቢ ሰብሳቢ ጽ/ቤት አልተላለፈም፤ እንዲሁም ለኢንቨስትመንት

መሬት ተረክበው ዓመታዊ የመሬት ኪራይ ካልከፈሉ 34 ባለሃብቶች በወቅቱ ያልተሰበሰበ ውዝፍ ኪራይ ብር 229,977.76 በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

31. በምዕራብ ጎጃም ዞን አስተዳደር ካሉ ወረዳዎች ከ2007 በጀት ዓመት ጀምሮ ለኢንቨስትመንት መሬት ከተረከቡ 22 ባለሃብቶች ብር 26,819,018.77 ዓመታዊ የመሬት ኪራይ ክፍያ ውዝፍ ሳይሰበሰብ ተገኝቷል፡፡

32. ሁኔታውም አጠቃላይ የክልሉን ኢንቨስትመንት በተፈለገዉ ፍጥነት ዕድገት እንዳያመጣ የሚያደርግ በመሆኑ ቢሮው ተገቢዉን ቅድመ ሁኔታ በማመቻቸት ወደ ተግባር እንዲገቡ የሚያስችል አሰራርን መተግበር እንደሚገባው እና መሰብሰብ ያለበት የመሬት ኪራይ ክፍያ እንዲሰበሰብና ወደ ስራ በማይገቡ ኢንቨስተሮች ላይ ተገቢዉ እርምጃ በወቅቱ መውሰድ እንደሚገባው ለተቋሙ በላክነው ሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

## የአብክመ መስኖ እና ቆላማ አካባቢዎች ልማት ቢሮ የመስኖ ግንባታ አፈጻጸምና ውጤታማነት፤

33. በክልሉ ውስጥ የተገነቡ ሁሉም የመስኖ ፕሮጀክቶች ያለማሉ ተብሎ የተቀመጠላቸውን ሄክታር መሬት ሙሉ በሙሉ የልማት አገልግሎት በመስጠት የታለማላቸውን አላማ ሊያሳኩ ሲገባ ሁሉም ፕሮጀክቶች የሚፈለገውን አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን ክትትል ተደርጎ መረጃዎችን የማጠናቀርና የፕሮጀክቶችን መምከን ለመታደግ የተዘረጋ አሰራር ባለመጠናከሩ አብዛኛዎቹ ፕሮጀክቶች የታለመላቸውን አገልግሎት በሙሉ አቅማቸው እየሰጡ አይደለም ፡፡ ለአብነትም በላይ ጋይንት ወረዳ 4፣ በፎገራ ወረዳ 4፣ በእስቴ ወረዳ 3 ፣ በአንዳቤት ወረዳ 1፣ በእብናት ወረዳ 2፣ በዚገም ወረዳ 1 በድምሩ 15 የመስኖ ፕሮጀክቶች ከ1996 እስከ 2010 ዓ.ም ባሉት ዓመታት ግንባታቸው ቢጠናቀቅም የኦዲት ሥራው እስከተጠናቀቀበት ግንቦት 2014 ዓ.ም ድረስ አገልግሎት መስጠት አልጀመሩም፡፡

34. በፋርጣ፣ በዳንግላ እና በዚገም ወረዳዎች የሚገኙ 3 የመስኖ ፕሮጀክቶች ከ2006 እስከ 2011 ዓ.ም ባሉት ዓመታት ግንባታቸው የተጠናቀቀና 286 ሄ/ር መሬት ያለማሉ ተብሎ

ይጠበቁ የነበረ ሲሆን በተጨባጭ ግን 59 ሄ/ር (20.6%) ብቻ ማልማት የቻሉ መሆኑን በኦዲት ምርመራ ወቅት ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

35. በዳንግላ ወረዳ የሚገኘው ውንብሪ አባይ የመስኖ ፕሮጀክትን አንድ ተቋራጭ በብር 51,762,743.06 በ2008 ዓ/ም ገንብቶ ለማስረከብ ውል ተወስዶ ብር 34,121,898.07 ወጭ ከሆነ በኋላ የካቲት 2010 ዓ/ም ላይ የግንባታ ስራው ሳይጠናቀቅ ተቋርጦ፣ እንደገና ለ2ኛ ተቋራጭ በብር 94,132,456.50 በ2013 ዓ/ም የተሰጠና መጋቢት 2014 ዓ/ም ገንብቶ ለማስረከብ ውል ወስዶ ብር 51,818,609.61 የተከፈለው ቢሆንም ኦዲት እስከተደረገበት ግንቦት 2014 ዓ.ም ድረስ ፕሮጀክቱ ያልተጠናቀቀና በድምሩ ብር 85,940,507.68 ወጭ የወጣበት መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

36. አምስት የመስኖ ፕሮጀክቶች ለግንባታቸው በድምሩ ብር 26,504,542 ክፍያ የተፈጸመ ቢሆንም ፕሮጀክቶቹ ያልተጠናቀቁና ውላቸውም የተቋረጠ መሆኑን በኦዲት ምርመራው ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በዝርዝር ለማሳየት ያክልም፡- በዚገም ወረዳ ለሚገኘው ላይኛው ዲም የመስኖ ፕሮጀክት ግንባታ ብር 3,324,131.94 ፣ በጉና በጌምድር ወረዳ በገንተኛ ቀበሌ ለሚገኘው ሀሙስ ወንዝ ዊር የመስኖ ፕሮጀክት ግንባታ ብር 10,334,684.96 ፣ በፋርጣ ወረዳ ገና ቀበሌ ለሚገኘው ሰባት ወደል የመስኖ ፕሮጀክት ግንባታ ብር 2,511,084.60፣ በደራ ወረዳ በቁላላ ቀበሌ ለሚገኘዉ ጣብቅ የመስኖ ፕሮጀክት ግንባታ ብር 8,427,113.47 እና በዳንግላ ወረዳ ምስራቅ ዘለሳ ቀበሌ ለሚገኘው አሻር የመስኖ ፕሮጀክት ብር1,907, 527.71 ናቸው፡፡

37. በመሆኑም ቢሮው በውል ለሚሰጣቸው መንግስታዊም ሆነ መንግስታዊ ላልሆኑ አካላት ውሉ በፍትህ ሊጸድቅና የግንባታ ስራዎችን በሚያጓትቱ ወይም በራሳቸው ጊዜ በሚያቆሙ ተቋራጮች ወይም ውል ተቀባዮች ላይ በውል ሰጪ በኩል ለሚደርሰው ኪሳራ እና ጉዳት ተገቢውን የጉዳት ካሳ ሊያገኝ እንደሚገባ በሪፖርታችን አስገንዝበናል፡፡

38. ኦዲት ተደራጊው መስሪያቤትም በግኝቱና በኦዲት አስተያየቱ ላይ ምላሽ የሰጠና ይህም የሚበረታታ ሲሆን በተገኙት ግኝቶችና በተሰጡት የኦዲት አስተያየቶች መነሻነት የማሻሻያ አሰራሮችን እንደሚቀይስና የክትትልና የድጋፍ ሥራዎችንም እንደሚያጠናክር በሰጠው ምላሽ አሳውቋል፡፡

**የተከበሩ አፈ-ጉባኤ!**

**የተከበሩ ርዕሰ መስተዳድር!**

**የተከበራችሁ የም/ቤት አባላት!**

**ጥሪ የተደረገላችሁ እንግዶች!**

**ክቡራትና ክቡራን!**

**መስሪያ ቤታችን ከዚህ ቀደም ኦዲት አድርጎ ባገኛቸው የኦዲት ግኝቶች ላይ በመመርኮዝ የኦዲት ተደራጊው አካል የወሰዳቸውን እርምጃዎች በክትትል ኦዲት የምናረጋግጥ ሲሆን ዉጤቱንም እንደሚከተለው አቀርባለሁ፡፡**

## የደብረ ብርሃን ከተማ ልማት ቤቶች ኮንስትራክሽን ጽ/ቤት እና ገቢዎች ጽ/ቤት የሊዝ ሂሳብ አስተዳደር ስርዓት

39. ከ2005 እስከ 2011 ዓ.ም በሊዝ ሂሳብ አስተዳደር ውጤታማነት ዙሪያ በተካሄደው የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት መነሻነት ኦዲት ተደራጊው ተቋማት በ43 (30.5%) ግኝቶች ላይ ሙሉ በሙሉ ማሻሻያ እርምጃ የተወሰደ ሲሆን በ6 (4.26 %) ግኝቶች ላይ በከፊል እርምጃ የተወሰደ ሲሆን፣ በቀሪዎቹ 92 (65.25%) ግኝቶች ላይ ግን ምንም ዓይነት የእርምት እርምጃ አልተወሰደም፡፡ የክትትል ኦዲቱ እስከተካሄደበት ሚያዝያ 2014 ዓ.ም ድረስ እርምጃ ሳይወሰድባቸው የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

39.1 አንድ የሊዝ ደንበኛ ለመኖሪያ አገልግሎት ቦታ በጨረታ ሸያጭ ያገኘውን ለሌላ ደንበኛ ሲያዛውር ለአዲሱ ደንበኛ በስማቸው በተዘጋጀዉ የዉል ስምምነት ሰነድ ላይ ቀሪ ክፍያ መያዝ ከነረበት ብር 52,877.78 በማነስ ዉል ተይዞ በተገኘው ላይ የማስተካካያ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤

39.2 አንድ ለንግድ አገልግሎት የተሰጠ ቦታ እና አምስት ለመኖሪያ አገልግሎት የተሰጡ በድምሩ ብር 9,228,000.00 የገንዘብ መጠን የያዙ ስድስት የሊዝ ደንበኛ ፋይሎች የውል ሰነድ ለኦዲት ስራ

እንዲቀርቡ በኦዲት ወቅት በተደጋጋሚ ተጠይቆ ሊቀርቡ ያልቻሉና አሁንም ያልተገኙ መሆናቸው፤

39.3 ከ2005 እስከ 2011 በጀት ዓመታት የአጭር ጊዜ ሊዝ መሬት ተረክበው ተጠቃሚ የሆኑትን የሊዝ ደንበኞች የቦታ አሰጣጥና የክፍያ ሁኔታ ለማጣራት የደንበኞች ዝርዝር ፋይል እንዲቀርብ ቢጠየቅም ከተማ አገልግሎቱ መረጃ የለኝም በማለቱ መረጃዉ በክትትል ኦዲትም ወቅት ሊቀርብ አለመቻሉ፤

39.4 ከ2005 እስከ 2011 ባሉት 7 በጀት ዓመታት በደ/ብርሃን ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት ላይ ዓመታዊ የሊዝ ክፍያ ካልከፈሉት 151 ደንበኞች ያልተሰበሰበ ጠቅላላ ዉዝፍ ሂሳብ ብር 5,581,272.46 ክትትል ኦዲቱ እስከተካሄደበት ጊዜ ድረስ ያልተሰበሰበና ከደንበኞቹ መካካል የ6ቱ በመመሪያው መሰረት ቦታቸዉን ሊነጠቁ የሚገባ ቢሆንም ምንም አይነት እርምጃ ሳይወሰድ መቅረቱ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸዉ፡፡

## ጐንደር ከተማ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ጽ/ቤት የመጠጥ ውሃ አቅርቦትና ንብረት አስተዳደር

40. ከ2008 እስከ 2012 ዓ.ም በተቋሙ የመጠጥ ዉሃ አቅርቦት እና ንብረት አስተዳደር ዙሪያ ኦዲት ተደርጎ በተሰጣቸው የክዋኔ የኦዲት ሪፖርት መሰረት ኦዲት ተደራጊው የጐንደር ከተማ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ጽ/ቤት በ40 (51.95%) ግኝቶች ላይ ሙሉ በሙሉ የማሻሻያ እርምጃ የወሰደ ሲሆን በ5(6.49%) ግኝቶች ላይ በከፊል እርምጃ ወስዷል፡፡ በቀሪዎቹ 32(41.56%) ግኝቶች ላይ ግን ምንም ዓይነት የእርምት እርምጃ ያልተወሰደ ሲሆን የክትትል ኦዲቱ እስከተካሄደበት ሚያዝያ 2014 ዓ.ም ድረስ እርምጃ ሳይወሰድባቸው የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

40.1 በአንገረብ የዉኃ ግድብ የውሃ ምርት ባልጨመረበት ሁኔታ ከተለመደዉ በላይ የኬሚካል አጠቃቀም በአይነት እና በመጠን ከአመት አመት እየጨመረ መሆኑ በኦዲት ተረጋግጦ ቢጠቆምም በክትትል ኦዲት ወቅትም ማስተካከያ ያልተደረገበት መሆኑ፤

40.2 ጽ/ቤቱ ለጎንደር ከተማ የመጠጥ ውሃ ለማቅረብ በቆላ ድባ ከተማ ያስቆፈራቸው 8 ጥልቅ ጉድጓዶች በቀን 17,000 ሜ.ኩ ውሃ ይሰጣሉ ተብለው ከ600 ሚሊዮን ብር በላይ ወጭ ተደርጎ

ቢገነቡም እየሰጡት ያለው የውሃ መጠን በቀን ከ3,000 ሜ.ኩ ያልበለጠ በመሆኑ ተቋሙ በገንዘብ በቀን ብር 231,000.00 በዓመት ብር 83,160,000.00 እንዳያገኝና ያለበትን ብድር ለመክፈል ከአቅሙ በላይ እንዲሆን ያደረገው መሆኑ በኦዲት ውጤቱ ቢጠቆምም የማሻሻያ እርምጃ ያልተወሰደበት መሆኑ፤

40.3 ከተለያዩ ደንበኞች ከ8 ዓመት በፊት ጀምሮ መሰብሰብ የነበረበት የውሃ ክፍያ ውዝፍ ሂሳብ ብር 1,351,445.15 ያልተሰበሰበ መሆኑ፤

40.4 ለጎንደር ከተማ የመጠጥ ውሃ ለማቅረብ ለ8 ጥልቅ ውሃ ጉድጓዶች እና ለተገነቡት 3 የግፊት ጣቢያዎች የኤሌክትሪክ ሃይል እንዲገባ በ2008 ዓ.ም ከኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ አገልግሎት የሰሜን ምዕራብ ሪጂን ጋር ሁለት ባለ160 kw፣ ሁለት ባለ 252 kw፣ ሁለት ባለ 400 kw፣ ሁለት ባለ 2000kw እና አንድ ባለ1240 kw የእቃና የእጅ ስራ ዋጋን ጨምሮ ለማቅረብ ውል ተይዞ ብር 32,043,031.36 የተከፈለ ቢሆንም ተገዝተው የቀረቡት እቃዎች ግን ምንም አይነት የገንዘብ ቅናሽ ሳይኖር የኃይል መጠናቸው የቀነሰ አራት ባለ37 kw እና አራት 93 kw እንዲቀርብ የተደረገ መሆኑ በኦዲት ሪፖርቱ የተጠቆመ ቢሆንም የተመለሰ ክፍያ አለመኖሩ፤

40.5 በአዘዞ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ በ2008 ዓ.ም በጉድለት የተገኙ የተለያዩ ንብረቶች ዋጋ ብር 115,813.48 እንዲተካ ያልተደረገ መሆኑ፣

40.6 በኦዲት ምርመራው ወቅት ያልተገኙ ግምታቸዉ ብር 164,244.96 የሆነ አሮጊ ቧንቧዎችና ሌሎች ንብረቶች እንዲተኩ ያልተደረገ መሆኑ፤

40.7 አንድ የጽ/ቤቱ ሰራተኛ በብልጫ የተወራረደ ነዳጅና የንብረት ጉድለት በድምሩ ብር 156,126.91 እያለባቸዉ የመንግስትን ገንዘብ ተመላሽ ሳያደርጉ ከስራ ገበታቸዉ የተሰናበቱና ገንዘቡ ያልተመለሰ መሆኑ የሚሉት ተጠቃሾች ናቸው፡፡

## አማራ መንገድ ስራዎች ድርጅት የግንባታ ሥራዎች፣ ግብዓት ግዢ፣ አቅርቦትና አስተዳደር

41. ከ2008 እስከ 2012 ዓ.ም በተቋሙ የግንባታ ስራዎች፤ግዥና የግብዓት አቅርቦት እና አስተዳደር ላይ የክዋኔ ኦዲት ተካሂዶ ለተቋሙ በተላከው የኦዲት ሪፖርት መነሻነት ኦዲት ተደራጊው አማራ መንገድ ስራዎች ድርጅት በ12 (30.77%) ግኝቶች ላይ ሙሉ ለሙሉ በ10 (25.64%) ግኝቶች ላይ በከፊል የእርምት እርምጃ ወስዷል፡፡ በቀሪዎቹ 17 (43.59%) ግኝቶች ላይ ግን ምንም አይነት የእርምት እርምጃ አልተወሰደም፡፡ የክትትል ኦዲቱ እስከተካሄደበት መስከረም 2015 ዓ.ም ድረስ እርምጃ ሳይወሰድባቸው ከተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች መካከል፡-

41.1 ድርጅቱ በሚያዚያ ወር 2012 ዓ.ም የቡሬ ኢንዱስትሪ መንደር የውስጥ ለውስጥ አስፓልት መንገድ ለመስራት ከአብክመ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ውል ወስዶ የአስፓልት የማንጠፍ ስራ ለቻይናው ተቋራጭ ለIFH ኢንጅነሪንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ ንዑስ ተቋራጭ በመስጠቱ ብር 22,292,145.40 ድርጅቱን ከያዘው ውል በላይ ለኪሳራ የዳረገ መሆኑና፡፡

41.2 የፕሮጀክቱ ንብረት የሆኑ ካት ዶዘርና ቮልቮ ኤክስካቫተር ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ ተበላሽተው በቆሙበት ቦታ እንዳሉ መሆናቸው ተጠቃሾች ናቸው፡፡

## አማራ ውኃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት የግንባታ አፈጻጸም፣የግዢና ሃብት አስተዳደር ሥርአት

42. ከ2007 እስከ 2012 ዓ.ም የፕሮጀክቶች ግንባታ አፈፃፀም እና የግዥና ሀብት አስተዳደር ስርዓት እንቅስቃሴ ዙሪያ በተካሄደው የክዋኔ ኦዲት በ19 (31.67%) ግኝቶች ላይ ሙሉ ለሙሉ የእርምት እርምጃ የተወሰደ ሲሆን በ13 (21.67%) ግኝቶች ላይ በከፊል እርምጃ ሲወሰድ በቀሪዎቹ 28 (46.67%) ግኝቶች ላይ ግን ምንም አይነት የእርምት እርምጃ አልተወሰደም፡፡ የክትትል ኦዲቱ እስከተካሄደበት ጥቅምት 2015 ዓ.ም ድረስ እርምጃ ሳይወሰድባቸው ከተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች መካከል፡-

42.1 ለአንድ ግዥ ከውል ስምምነት ውጭ በድርጅቱ አለአግባብ በድጋሜ የተከፈለ ብር 16,652,845.79 በተጨባጭ እስከአሁን የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩ፤

42.2 ዋጋቸው ብር 1,945,754.00 የሆነ 4,120 የቧንቧ መገጣጠሚያዎች ለድርጅቱ ባልደረሱበት ሁኔታ አላግባብ የተፈጸመ ክፍያ በተጨባጭ እስከአሁን የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩ፤

42.3 ብዛታቸው 322 የሆኑ ቧንቧዎች ወደ ድርጅቱ ገቢ ሳይደረጉ የተፈጸመ ክፍያ ብር 359,394.55 በተጨባጭ እስከአሁን የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩ፤

42.4 የጣና በለስ ሜጋ ፕሮጀክት ከኢትዮጵያ ብረታ ብረት ኢንጅነሪንግ / ሜቴክ / ጋር በተዋዋለዉ የዉል ስምምነት መሰረት ለግንባታ ስራ አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችን የስራ ቦታዉ ላይ / material on site / ገዝቶ ብር 16,329,889.93 የሚያወጡ የግንባታ ቁሳቁሶች ቢያቀርብም ገንዘቡ ያልተከፈለዉ መሆኑ፤

42.5 ድርጅቱ በየካቲት 2003 ዓ.ም በቀጥታ የግዥ ዘዴ ከኢፌድሪ ብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን (ሜቴክ ) በብር 5,500,000 ተገዝቶ ወደ ድርጅቱ የገባዉ የባችንግ ፕላንት ማሽን የማይሰራና ለ8 ዓመታት ያህል በጣና በለስ ፕሮጀክት ተተክሎ አገልግሎት እየሰጠ አለመሆኑ፣

42.6 ከ2005 እስከ 2007 ዓ.ም ለሞጣ መጠጥ ዉሃ ፕሮጀክት ስራ ላይ ከዋሉት ጥሬ እቃዎች ዉስጥ ብር 1,138,264.06 የሚያወጡ 2,619.44 ሜትር ርዝመት ያላቸዉ ቧንቧዎችና ብዛታቸዉ 780 የሆኑ የተለያዩ ፊቲንጎች ለአገልግሎት ከዋለዉ በላይ በብልጫ ወጭ ተደርገዉ ወደ ንብረት ክፍል ሳይመለሱ የቀሩ መሆኑ የሚሉት ናቸዉ።

## ማጠቃለያ

በአጠቃላይ በመስሪያቤታችን የክዋኔ ኦዲት የተካሄደባቸው መ/ቤቶች በኦዲቱ የታዩትን ክፍተቶች መነሻ በማድረግና ተገቢ የሆነ ትኩረት በመስጠት የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰዱ፣ በቀጣይም ለሚካሄዱ ተግባራት እንደ መነሻ በመወሰድ ተመሳሳይ ክፍተቶች እንዳይከሰቱ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባቸው ለኦዲት ተደራጊ ተቋማት በየሪፖርታቸው በዝርዝር አሳስበናል፡፡

ስለሆነም በኦዲቱ የተመለከቱትን ግኝቶችና የአሰራር ክፍተቶች በማረም ተጠያቂነትንና መልካም አስተዳደርን በማስፈን ረገድ ኦዲቱ እሴት እንዲጨምር በኦዲት ማሻሻያ አስተያየቶች መሰረት ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ በሚመለከታቸው አካላትና በም/ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች በኩል ክትትል እንዲደረግባቸው እያሳሰብኩ የተከበሩ አፈ-ጉባዔ፤ የም/ቤት አባላት፤ የበጀትና የፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴና ሌሎች ቋሚ ኮሚቴዎች፤ የፍትህ አካላትና ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች በስራ ሂደት ላደረጋችሁልን የስራ ትብብር እንዲሁም የመ/ቤታችን ባለሙያዎች በዚህ ሪፖርት ለተመላከቱ የስራ ውጤቶች ላደረጋችሁት ጥረት በራሴና በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ዋና ኦዲተር መ/ቤት ስም ምስጋናዬን በማቅረብ ሪፖርቱን በዚህ አጠናቅቃለሁ፡፡

**“አመሰግናለሁ”**

**አማረ ብርሃኑ (ዶ/ር)**

**ዋና ኦዲተር**